# የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ የርቀት ትምህርት የዕውቅና እና የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አሰጣጥ መመሪያ

ትምህርት ሚኒስቴር

ሐምሌ 2004

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. መግቢያ

በኤፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀፅ 97/2 እንዲሁም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 30 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት እና ጥራትን ለማስጠበቅ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ የርቀት ከፍተኛ ትምህርት የዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ 2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፦

1) "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው።
2) "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው።
3) "ኤጀንሲ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው።
4) "የከፍተኛ ትምህርት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 8 የተመለከተውን ትርጉም ይይዛል።
5) "ተቋም" ማለት የከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ የመንግሥት፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ነው።
6) " የርቀት ትምህርት" ማለት በመደበኛ ወይም በአካል (ገጽ ለገጽ) ከሚሰጥ መርሃግብር ውጭ የሚሰጥ ከፍተኛ ትምህርት ነው።
7) "የርቀት ትምህርት ዕውቅና ፈቃድ" ማለት የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ለመጀመር በአዋጁ መሰረት ለተቋም ለ 3 ዓመት የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው።
8) "የርቀት ትምህርት ዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት" ማለት የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና እንዲቀጥል በአዋጁ መሰረት ለ 5 ዓመት ለተቋም የሚሰጥ የእድሳት ፈቃድ ነው።
9) "ሞዱዩል" ማለት አንድን ትምህርት (ኮርስን) ለማስተማር የሚረዳ ለኮርሱ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱ ይዘቶችን የያዘና ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጨብጡ የሚያስችል የትምህርት መርጃ ነው።

10) "የማጣቀሻ መጽሐፍ" (Reference book) ማለት ሊሰጥ ለታሰበው ትምህርት (ኮርስ) የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል መጽሐፍ ነው።
11) "ሳይንቲፊክ ጆርናል" ማለት ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶች የሚታተሙበት ታዋቂ መጽሔት ነው።
12) "የሪሶርስ ማዕከል" (Resource Center) ማለት ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጥ በውስጡ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ያሉት ክፍል ነው።
13) "ዋና ማዕከል" ማለት ሁሉንም ቅርንጫፍ ማዕከላት የሚያስተባብርና የሚቆጣጠር ማለት ነው።
14) "ቅርንጫፍ ማዕከል" ማለት ትምህርቱ በሚሰጥበት አካባቢ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያስተባብርና የሚቆጣጠር ማለት ነው።
15) "ተግባር ተኮር ትምህርት" ማለት ቤተሙከራ፣ ዴሞንስትሬሽን፣ ወርክሾፕና የመሳሰሉትን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ትምህርት ነው።
16) "ቱተር" ማለት በርቀት ትምህርት ፕሮግራም የሚሳተፉ ተማሪዎችን በየደረጃዉ የአካዳሚክ ድጋፍ እና በሌሎችም ማህበራዊ ችግሮች ተገቢውን ምክር የሚሰጥ ባለሙያ ነው።
17) "የማስተካከያ እርምጃ" እንዳስፈላጊነቱ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ወይም የእውቅና ፈቃድን መሰረዝ ማለት ነው።

# ክፍል ሁለት

## በርቀት ስልት ለሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት የእውቅና እና የእውቅና ፈቃድ ዕድሳት ለማስተናገድ የሚያገለግሉ መሰረታዊ ጉዳዮች (92180)

### 4. መርሆዎች

በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ተፈጻሚነት ያላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በተለይም

1) ማንኛውም ተቋም ተማሪዎችን የሚቀበልበት ሥርዓት በሃይማኖት፣ በብሔር በፆታና በመደብ ልዩነት የማይደረግበት ይሆናል።
2) ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው ከሃይማኖት ነፃ የሆነ ወይም ሴኩላር መሆን ይኖርበታል።
3) የቋንቋ ሥልጠናዎች በሚሰጡበት ጊዜ ሥልጠናው በዚያ ቋንቋ የሚሰጥ ይሆናል። ከዚህ በስተቀር የማንኛውም ተቋም የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል።
4) የዕውቅና ፈቃድ የሚጠየቅባቸው ስልጠና መስኮች ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ሆኖ ተግባር ተኮር ባልሆኑ የስልጠና መስኮች ይሆናል።
5) ማንኛውም ተቋም ማስተማር የሚችለው የዕውቅና ፈቃድ እና የዕውቅና ፈቃድ እድሳት በተሰጠው የስልጠና መስክ እና ተገምግመው ብቃታቸው በተረጋገጠባቸው ዋና ማዕከልና ቅርንጫፍ ማዕከላት ብቻ ይሆናል።
6) ማንኛውም ተቋም ለተማሪዎቹ የገጽ ለገጽ (tutorial class) ክፍለ ጊዜ ማግኘት የሚችሉበትን የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር አለበት።
7) የተቋሙ ስያሜ በአዋጁ ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት እና ኤጀንሲው ለዚሁ የሚያወጣውን የማስፈጸሚያ መመሪያ መሰረት ያደረገ ይሆናል።
8) ተቋሙ የሚያካሂደው የምርምር ሥራ የአገሪቱን እድገትና ልማት የሚያፋጥን፣ የሚያስቀጥልና ችግር ፈቺ መሆን ይኖርበታል።
9) ተቋሙ የመደበኛ መርሀግብር የሚሰጥ ከሆነ ለርቀት መርሀግብሩ ራሱን የቻለ ተቋማዊ አደረጃጀትና ስርዓት ይኖረዋል።
10) ተቋሙ የአገሪቱን የትምህርት ካሌንደር ተከትሎ በሶስት ተርሞች የአዲስ ተማሪ ምዝገባ በማካሄድ ስልጠና መስጠት ይችላል። ነገር ግን ትምህርቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ በአንድ ተርም ሊወሰድ የሚገባውን ከ9 እስከ 12 ክሬዲት አወር ባገናዘበ መልኩ ይሆናል።
11) በርቀት ስልት የሚሰጠው ትምህርት የጥራት ደረጃ በመደበኛ ከሚሰጠው ተለይቶ አይታይም።
12) የርቀት የትምህርት አሰጣጥ ስልት በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ግብዓት ሊደገፍ ይገባል።

## 5. የተማሪዎች ቅበላ

ማንኛውም ተቋም ተማሪዎችን የሚቀበለው በአዋጁ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ 3 (ሀ) እና (ሐ) በተደነገገው መሰረት

1) የመሰናዶ ትምህርት ያጠናቀቁትንና ሚኒስቴሩ የሚያስቀምጠውን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የማለፊያ ነጥብ የሚያሟሉትን፣
2) በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በኤጀንሲው የአቻ ግምት የተሰጣቸውን፣
3) ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፍ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመሸጋገሪያ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟሉትን፣
4) ተቀባይነቱ የተረጋገጠ ሌላ ዲግሪ ያላቸውን፣
5) ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ የሚያሟሉ ጎልማሶችን

ይሆናል።

## 6. ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው የሚሰጥበት ማዕከልና ከባቢ (surrounding) ሁኔታ

1) ትምህርቱን ወይም ሥልጠናው የሚሰጥበት ሕንፃና ግቢ በተቋሙ በግል ንብረትነት የተያዘ ወይም በማናቸውም በሕግ ፊት ሊጸና በሚችል ውል ከ3-5 ዓመታት እንዲያገለግል በኪራይ የተያዘ እና ማዕከላቱ የስልጠናውን ሂደት ለሚያውኩ ሁኔታዎች ባልተጋለጠ ከባቢ መሆናቸው፣
2) ዋናው እና ቅርንጫፍ ማዕከላቱ የሚገኙበት ቦታ የመሬት አቀማመጥ ለጎርፍ፣ ለከባድ ንፋስ፣ ለፍሳሽና ሌሎች አደጋዎች ያልተጋለጠና ምቹ የመኪና መንገድ ያለው መሆኑ፤
3) የተቋሙ ለሰራተኞችና ለተማሪዎች ሊያገለግሉ የሚችሉ የመጸዳጃ ክፍሎች እና የመጀመርያ ሕክምና እርዳታ መስጫ ኪት ያሉት ይሆናል።

## 7. ክፍያ

የዕውቅናና የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በመንግሥት በጸደቀ ተመን መሰረት ይሆናል።

## 8. የዕውቅናና ዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አስፈላጊነት

1) የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ፣ ለመለወጥ ወይም ዕውቅና በተሰጠው ለመቀጠል ወይም አዲስ የትምህርት ዓይነት ለመክፈት የሚፈልግ ማንኛውም ተቋም በአዋጁና በዚህ መመሪያ የዕውቅና ፈቃድ ሳያገኝ የከፍተኛ ትምህርት ሊሰጥ አይችልም።

2) በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በርቀት ስልት ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም በዚህ መመሪያ የዕውቅና ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

## ክፍል ሶስት

## የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መገምገሚያ መስፈርቶችና ነጥቦች

### 10. የዕውቅና ፈቃድ አገልግሎት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

በርቀት ስልት ትምህርት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም እና የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ ወይም ተጨማሪ ማዕከል ለመክፈት ወይም አዲስ የስልጠና መስክ ለመክፈት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ የዕውቅና ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል። የሚቀርበው ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 75 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ

1) ለተቋሙ ደረጃ የሚመጥን አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት፣
2) ተቋሙ ለሚያቀርበው የደረጃ ስያሜ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣
3) በማመልከቻ ቅጹ ላይ የተመለከቱ ግብዓት መሟላታቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች፣
4) የሕንጻ የይዞታ ማስረጃ ወይም የኪራይ ውል ማቅረብ ይኖርበታል።

### 11. የዕውቅና ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት የተዘጋጀ ተቋም ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው።

የርቀት ትምህርት የዕውቅና ፈቃድ ለማግኘት ተቋሙ ፈቃዱን በጠየቀበት በእያንዳንዱ መርሃግብር የርቀት ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ባዘጋጃቸው ጣቢያዎች በሙሉ የተሟሉና በማመልከቻ ቅፁ መሰረት ለተማሪው አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የተደራጁ ማዕከላት ሊኖረው ይገባል።

1) ተቋሙ በአንድ የትምህርት ዘመን ከተፈቀደለት የትምህርት መስክና ማዕከል ውጭ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማሰልጠን የሚጠበቀውን መስፈርት በማሟላት ትምህርትና ስልጠና ከመጀመሩ በፊት ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።
2) የተቋሙ አመራርና አደረጃጀት

ሀ) በዲግሪ ደረጃ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል፣ ግልጽና የመማር ማስተማር፣ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው አደረጃጀት (Senate/ Academic Commission, Department council…) ሊኖረው ይገባል።

ለ) ለዲግሪ ፕሮግራም ራሱን የቻለ አደረጃጀትና የአስተዳደር ስርዓት ያለው፣

ሐ) ደረጃውን የጠበቀ ሞጁዩል፣ የቱተሮች አመላመልና አቀጣጠር ስርዓት፣ የማዕከል አስተባባሪ የትምህርት ደረጃ እና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቁጥርና የትምህርት ደረጃ፣

መ) ተቋሙ በየዓመቱ ሊያከናውን ያቀዳቸው ስራዎች፣

ሠ) የተቋሙ በጀት ለሚሰጠው ግልጋሎት በቂና አስተማማኝ የሆነ፣

ረ) በተቋሙ አደረጃጀት መሰረት በስልጠናውና በአገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እና

ሰ) ለፕሮግራሙ መሳካት የተሰማሩ ሰራተኞች የሥራ ድርሻ በጽሁፍ በተደገፈ ሰነድ የተቀመጠ

መሆን ይኖርበታል።

## 3) ሞጁዩልን በተመለከተ

ሀ) የማስተማሪያ ጽሑፎች (ሞጁዩሎች) ለተጠቃሚው ትምህርት አቀባበል የሚያመቹ (User Friendly) ሆነው በተሟላ መልኩ መዘጋጀት አለባቸው።

ለ) በእያንዳንዱ የዲግሪ መርሃግብር የሚሠጡ ኮርሶች እንደየመርሃግብሩ የስልጠና ጊዜ ርዝማኔ በብቃት ለማስተማርና ለማሠልጠን የሚረዱ ሞዱሎች መዘጋጀት አለባቸው።

ሐ) የእያንዳንዱ ኮርስ ሞጁዩል ደረጃውን የጠበቀ የአዘገጃጀት መመሪያን በተከተለ መልኩ ሞጁዩል የማዘጋጀት ልምድ ባላቸው መምህራን ተዘጋጅቶ እና የተሻለ የአካዳሚክ ደረጃና የማስተማር ልምድ ባላቸው መምህራን ዳብሮ መታተም ይኖርበታል።

መ) በየዩኒቶቹ ማብቂያ ላይ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲገመግሙ የሚያስችላቸው መልመጃዎች ሊኖሩ ይገባል።

## 4) ቱተሮችን በተመለከተ

ሀ) ለእያንዳንዱ የስልጠና መስክ ለቱቶሪያል አገልግሎት የሚመለመል ቱተር ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ወይም ተመሳሳይ የአካዳሚክ ደረጃ ሊኖረው ይገባል።

ለ) ቱቶሩ በተቋሙ የማወዳደሪያ መስፈርት የተመረጠ መሆን አለበት።

ሐ) እያንዳንዱ ቱቶር ለተማሪዎች አገልግሎት መስጠት ያለበት በሰለጠነበት የሙያ መስክ ብቻ ይሆናል።

መ) የገጽ ለገጽ ገለጻውን ውጤታማ በሆነ መልክ ለመተግበር ለ50 ተማሪዎች የአንድ ቱተር ምጣኔ ሊኖር ይገባል።

ሠ) ቱተሮች በገጽ ለገጽ ገለጻ (tutorial) አሰጣጥና ሞዲዮል አጠቃቀም ላይ ስልጠና ሊወስዱ ይገባል።

## 5) የገጽ ለገጽ (tutorial) የትምህርት አሰጣጥን በተመለከተ

ሀ) የገጽ ለገጽ ትምህርት አገልግሎት የሚሰጠው አመቺ በሆኑ ቦታዎች ይሆናል። ነገር ግን ተማሪው ቀደም ብለው እንዲያውቅ በተደረጉ ቦታዎች እንዲሁም ፈቃድ በተሰጠባቸው ቅርንጫፍ ማዕከላት ብቻ ይሆናል።

ለ) ማንኛውም የርቀት ትምህርት የሚያካሂድ ተቋም በተርም ሁለት ጊዜ ለእያንዳንዱ ኮርስ ተማሪዎች ከቱተሮች ጋር የሚገናኙበት ከ2-3 ሰዓት ርዝማኔ ያለው የገጽ ለገጽ ትምህርት አገልግሎት ፕሮግራም ማዘጋጀት አለበት።

ሐ) ተማሪዎች የቱቶሪያል ፕሮግራሞቹን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስለመሳተፋቸው መረጃ ሊያዝ ይገባል።

መ) ተማሪዎች የማጠቃለያ ፈተና ከመውሰዳቸዉ በፊት የቱቶሪያል ክፍለ ጊዜዎችን እንዲሳተፉ ተቋሙ ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል።

ሠ) የትምህርት አሰጣጡ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ግብዓቶች (ሲዲ፣ ኢንተርኔት፣ ኢሜይል፣ ወዘተ) ሊደገፍ ይገባል።

## 6) የርቀት ትምህርት የስልጠና ጊዜ ቆይታን (duration) በተመለከተ

ሀ) በርቀት ትምህርት አሰጣጥ አንድ የትምህርት ዘመን (academic year) 3 ተርሞች ሊኖረው ይችላል።

ለ) በአንድ ተርም (3 ወራት) ጊዜ ውስጥ ከ9-12 ክሬዲት አወር ያልበለጠ መስጠት ይገባል።

ሐ) የ3 ዓመት የመደበኛ የስልጠና ጊዜ የሚፈጅ ስልጠና በርቀት መርሃግብር ከ3 ዓመት ባነሰ ጊዜ ሊጠናቀቅ አይገባም።

መ) አንድ ተማሪ የቀዳሚውን ተርም ውጤት ከማወቁ በፊት ለቀጣዩ ተርም ሊመዘገብ አይገባም።

## 7) የርቀት ትምህርት የዋናና የቅርንጫፍ ማዕከላት ኃላፊዎችን በተመለከተ

ሀ) የዋና ማዕከል ኃላፊ የማስተርስ ዲግሪ እና የቅርንጫፍ ማዕከላት ኃላፊዎች ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁና በማስተማር ሙያ ልምድ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

ለ) የማዕከላቱ ኃላፊዎች ብቃትን መሰረት ባደረገ የውድድር ስርዓት ሊመለመሉ ይገባል።

## 8) የምዘናና የፈተና አሰጣጥን በተመለከተ

ሀ) ተቋሙ/ማዕከሉ የምዘናና የፈተና አሰጣጡ የሚመራበት መመሪያ ሊኖረው ይገባል።

ለ) በየኮርሶች ማብቂያ ላይ ቁጥጥር የሚደረግበት የማጠቃለያ ፈተና መስጠት አለበት።

ሐ) ፈተናዎች በዋና ማዕከሉ ተዘጋጅተው ለቅርንጫፍ ማዕከላት ታሽገው፣ ተፈርሞባቸውና ማህተም ተደርጎባቸው መሰራጨት ይኖርባቸዋል።

መ) ፈተናው አስተማማኝና ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ተቀምጦ ለተፈታኞች የሚደርስበት ስርዓትና አሰራር ተዘርግቶ ሊተገበር ይገባል።

ሠ) በፈተና ወቅት እያንዳንዱ ተፈታኝ የተቋሙን መታወቂያ በማሳየት ስለመፈተኑ ማረጋገጫ ሊኖር ይገባል።

ረ) ፈተና በሚሰጥባቸው ክፍሎች አንድ ፈታኝ ለ30 ተፈታኞች ምጣኔ የሚመደቡበትና ተገቢ የሆነ ክትትል የሚደረግበት ሊሆን ይገባል።

ሰ) የፕሮጀክትና የአሳይንመንት ምዘናዎች በአግባቡ ሊመዘገቡና ሊያዙ ይገባል።

ሸ) የውጤት አሰጣጡ የተቋሙን የውስጥ ደንብና መመሪያ መሰረት በማድረግ መፈጸም አለበት።

ቀ) የእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት የሚቀጥለው ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ለተማሪዎች ሊገለጽ ይገባል።

በ) በውጤት ላይ ለሚኖር ቅሬታ የአቀራረብና አፈታት ስርዓት መኖር አለበት።

## 9) የተቋሙን ፊዚካል ግብዓቶች በተመለከተ

ሀ) አንድ የርቀት ትምህርት የሚያካሂድ ተቋም በዋና ማዕከሉ ስራውን የሚመራበት የስራ ኃላፊዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለጥራት ማስጠበቂያ ዩኒት፣ የሞጁዩል ዝግጅትና ስርጭት የፈተና ዝግጅትና አስተዳደር፣ የየትምህርት ክፍል ማስተባበሪያዎች፣ የተማሪዎች አገልግሎት፣ የቤተ መጻሕፍት፣ የትራንስፖርት፣ የፀሐፊዎችና የሬጅስትራር ቢሮዎች ከተሟሉ የቢሮ ቁሳቁሶች ጋር እንዲኖሩት ያስፈልጋል።

ለ) በቅርንጫፍ ማዕከላት ለርቀት ትምህርት ኃላፊው፣ ለተማሪዎች የምክርና ድጋፍ አገልግሎት፣ ለቤተመጻሕፍት፣ ለሞጁዩል ስርጭት፣ ለኮምፒዩተር ክፍል፣ ለቅድመ ቅበላ (registration) እና የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የሚሆኑ ቢሮዎች ከተሟሉ የቢሮ ቁሳቁሶች ጋር እንዲኖሩት ያስፈልጋል።

ሐ) የርቀት ትምህርትን ከመደበኛው በተጓዳኝ አብሮ የሚያካሂድ ተቋም ከላይ የተጠቀሱትን ፋሲሊቲዎች ለርቀት ትምህርት በሚሆን መልኩ መጠቀም መቻሉን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

### 10) የመገናኛ ዘዴዎች

ቅርንጫፍ ማዕከላት ከዋናው ማዕከል ጋር የሚገናኙበት የስልክ፣ የፋክስ፣ የፖስታ፣ ኢሜይል ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት አገልግሎቶች እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

### 11) የትምህርት ማዕከል (Resource Center)

ሀ) እያንዳንዱ ተቋም እንደ ተማሪዎቹ ብዛት በቂ የቱቶሪያል ማዕከላትን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

ለ) እያንዳንዱ የርቀት ትምህርት ተቋም በቅርንጫፍ ማዕከሉ ካሉት ተማሪዎች 5% በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል የተሟላ ሚኒ ላይብራሪ (የማጣቀሻ መጽሐፍት) በማደራጀት አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል።

ሐ) ማንኛውም ተቋም እንደየስልጠና መስኩ ተማሪዎች ከሞጁዩል በተጨማሪ ለየኮርሶቹ የተዘጋጁ ቪዲዮ ካሴቶች፣ ሲዲዎች፣ ኦዲዮ ካሴት ወ.ዘ.ተ. እንዲሁም የኢንተርኔት አገልግሎት ሊያደራጅ ይገባል።

መ) በርቀት ስልት ትምህርት የሚሰጥ ተቋም ለየኮርሱ የተማሪውን ቁጥር ግምት ውስጥ በማስገባት በበቂ ኮፒ የማስተማሪያ መጻሕፍት (Modules)፣ የማጣቀሻ መጻሕፍት፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ሳይንሳዊ ጆርናሎች (በየስልጠና መስኩ) እንዲሁም ኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍት ሊኖረው ይገባል።

## 12. የርቀት ትምህርት የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

ኤጀንሲው በአንቀጽ 11 የተቀመጡት መመዘኛዎች መሟላታቸውን ገምግሞ በማረጋገጥ የዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል።

# ክፍል አራት
# የርቀት ትምህርት ዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አሰጣጥ መገምገሚያ
# መስፈርቶችና ነጥቦች

## 13. የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ፣

1) የርቀት ትምህርት የዕውቅና ፈቃድ እድሳት ለማግኘት ተቋሙ ፈቃዱን በጠየቀባቸው በእያንዳንዱ መርሃግብር በአንቀጽ 12 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች በዋነኛነት የሚታዩ ናቸው፣

   ሀ) በኤጀንሲው የጥራት ኦዲት መመሪያ መሰረት ተቋማዊ ግምገማ በማድረግ የግለ ግምገማ ሰነድ (Self Evaluation Document) በማዘጋጀት የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ ከማቅረቡ ከአንድ ዓመት በፊት ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት።

   ለ) እውቅና ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ የተደረጉ ማሻሻያዎች/ማስተካከያዎችን የሚያሳይ መረጃ መቅረብ አለበት።

   ሐ) በየዓመቱ ከተያዘው እቅድ በመነሳት የአፈጻጸም ሪፖርት መላክ ይኖርበታል።

## 14. የርቀት ትምህርት የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ስለመስጠት

1) ኤጀንሲው በተቋሙ የቀረበውን ግለ-ግምገማ ሰነድና፣ ሌሎች ሪፖርቶችን በመመርመር፤ በነዚሁ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎችንና ስታትስቲካዊ መግለጫዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣
2) በተቋሙ የሚሰጡ የስልጠና መስኮችን ባገናዘበ መልክ የተቋሙን አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ መሰረተ ልማቶች፣ ሞጁዩሎችን፣ የመማር ማስተማር ሂደትን፣ የተማሪዎች መረጃዎችን፣ የትምህርት መገልገያዎችን፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና የቱቶሮችን ብቃትን ጨምሮ የተማሪዎች የትምህርቱ ጥራት ግምገማን፣ የማዕከል አስተባባሪንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ዝርዝርና የትምህርት ደረጃን በጥልቀት በመገምገም ፈቃዱ ይታደስለታል።

## 15. ሌሎች የአዋጁን ድንጋጌዎች በተመለከተ

የእውቅና ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ የዕውቅና ፈቃድ ስለመከልከል፣ የእውቅና ፈቃድ እና የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ያገኙ ተቋማትን ስለማሳወቅ እና አቤቱታ ማቅረብን በተመለከተ በአዋጁ አግባብነት ባላቸው አንቀጾች በተደነገገው መሰረት ይሆናል።

## 16. ኃላፊነት

1) ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም የግል ተቋም ላይ ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።
2) ከአዋጁና ከዚህ መመሪያ ውጭ የተገኘ የትምህርት ማስረጃ ተቀባይነት የለውም።

## 17. ስለ ማሻሻያ

አውጪው ባለሥልጣን ይህን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሊያሻሽል ይችላል።

## 18. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በማንኛውም ተቋም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።